# ከኃይለሥላሴ ጉግሳ እስከ ዶክተር ዜሮ
# ከገላውዲዮስ አርአያ እስከ ስየ አብርሀ

አውግቸው ብሩ

ቅዱስ መፅሀፍ ትንሳዔ ለፅድቅ፤ ትንሳዔ ለፍርድ የሚለው ጉዳይ አለ ። ዓለም ስትፈፀምና የተንስኡ ነጋሪት ሲጎሰም ሁሉም ነፍስ ሲነሳ-ሲሰለፍ ለፍርድ የሚነሱ የሚቀርቡ ብዙ ናቸው። ግን ያውቁታል ማለት አይደለም። ባለፈው ሰሞን የቀይ ሽብር ነፍሰ ገዳዮችና የደርግ ሚሊሺያና ካድሬዎች በሞሉበት አንድ ፓልቶክ በቀይ ሽብር የተጠቁት ራሳቸው ይቅርታ ይጠይቁ የሚል ፅሁፍ ቀርቦ ነበር። ያቺ የፍርድ ቀን ስትመጣ አንጃ ግራንጃውም፤ በታኙም ቅጥረኛውም፤ ወገኑን የከዳው ሁሉ ለፍርድ ይቀርባል። ንስሐ ቢቀድም ጨው ለራሱ ሲል ጣፈጠ በሆነ ነበር።

ኢትዮጵያ ያሸበረቀና የሚያኮራ ታሪክ እንዳላት ሁሉ የታሪክ አንዳንድ ገፅታዋ ደግሞ ፈንጣጣ እንዳጠቃው ፊት የተበሳሳ ወይም እንደ ከረመ አስከሬን የማያምር ነው። ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ የባንዳ ምሳሌ ቢሆንም ደጃዝማች ገብረሥላሴም ቢሆኑ ለጣሊያን ባንዳ ለመሆን የፃፉትን የማመልከቻ ደብዳቤ የታሪክ መምህሩ ፕሮፌሰር ዓለም እሸቴ በኮፒ አሰራጭቶ/አሳትሞ አሳውቆናል፡፡ ብዙ ሀገሩን የከዳ ባንዳ፤ አርበኞችን በጅርባ ያጠቃ፤ ያጋለጠ ፤ያስመታና የመታ ከሀዲ ነበር። በቅርቡ የሞተው ዜናዊ አባቱ አስረሱ የጣሊያን ባንዳ ነበር። በታሪክ የጀግኖቹ ገድል ወደ ተከታዩ ትውልድ እንደወረደው ሁሉ የባንዳውም ቅርስ ተላልፏል። ከአስረሱ ወደ ለገሰ /መለስ ደርሰናል። ሀገርና ወገንን የሚከዱ ትላንትም ሆነ ዛሬ በዚህም በዚያም ይርመሰመሳሉ። በአፄ ኃይለሥላዜ ጊዜ ብዙ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች በከሀዲዎች ተጨናግፏል። በዘመነ ደርግም ከዚያ ፋሺስታዊ አረመኔ ቡድን ጋር ሆነው ትውልድን ያረዱ ነፍስገዳዮችና ከሀዲዎች (ዛሬ በአሜሪካ ምድር ብዙ ናቸው) ከጣሊያን ጊዜ ባንዳ የሚለዩ አይደሉም። ዘመናዊ ባንዳ የሚለው ስያሜም ቦታና ትርጉም የነበረው ለዚሁ ነው። በኢሕአፓ ተመክሮ ደግሞ አንጃ የሆነው ቡድን ድርጅቱን አሳልፎ ሰጥቶ ይህ ነው የማይባል ጉዳትን አስከትሏል። ድርጅቱን ጓዶቹን ክዶ ለደርጉ አገልጋይ ባንዳ ሆኗል። የአንጃው ሌላ ፀያፍ ገፅታ ደግሞ በታኝነት ነው። ይህም በዶክተር ዜሮና መሰሎቹ ሁለት ጊዜ በኢሕአፓ ላይ ተሞክሯል። ይህ የነቃ የበቃ የተባለ ድርጅት ነጋ ጠባ እንግዳ ያልሆኑ የሆኑ በታኞች እንዴት ይጫወቱበታል? በሜዳው አንጃ የዛሬው የቅንጅት አንጃ መሪ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የነበረበት ሲሆን በዛሬው የኢሕአፓ አንጃ ደግሞ ብተናን ካካሄዱት ቀንደኛው የነበረውናፀረ ኢሕአፓነቱ  ሞልቶ የፈሰሰበት ዶክተር ዜሮ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

አንዳንዶች ለምን ወደ ግለሰቦች ታሪካዊ ሀቅ ትመለሳላችሁ ሲሉ ያማርራሉ። ያ የአበው ተረት እንደሚለው ጅብ በማይታወቅበት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ያለውን አስታውሰን ነው። የከፋ ታሪካቸውን ደብቀው፤ ይባስ ብለው በሌባ ዓይነ ደረቅነት ሰለባቸውን የሚከሱ፤ ድርጊታቸውን ሸፍነው በሌላ የሚላክኩ እንዳያወናብዱ ማድረግ የምንችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። በቅድሚያ ነፍሰ ገዳዮች ለፍርድ መቅረብ አለባቸው። የሀገራችን የመጀመሪያ ጠላት ወያኔ ነው ብለን ዝም ብንላቸው የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ይባስ ብለው ከሳሽና አውጋዥ

ሊሆኑ ተነሱ፡፡ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ለምን የአንጃ ደጋፊ ሆኑ ስንልም ሌሎች ጥያቄዎችን ማንሳት እንገደዳለን፡፡ በቀልቤሳ የደረሰው መደገም አለበት፡፡ በወንጀለኞች ላይ ዘመቻው መፋፋም ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ሌላ የሕዝባችን ትግል ቀና መንገድ ይዞ እንዲጠናከር ከተፈለገ  ትግሉን የሚያደናቅፉትን መሰሪዎች ማንነት አጋልጦ ማግለል ተገቢ ነው፡፡ ዶክተር ብርሃኑ የሕዝብን ትግል ሲያደናቅፍ ቆይቶ ዛሬ በረቀቀ መንገድ የትጥቅ ትግል ጥሪትን ሊያበላሽ ሲሞክር በዝምታ ልናልፈው አንችልም፡፡ በለንደንና ሌሎች የአውሮጳ ከተሞች ገኖ የነበረውን የቅንጅት እንቅስቃሴ  በሻጥር አፈር ያበላውን ሀ ሲባል የአማራውን ሕዝብ ለወያኔ ሰለባ ያቀረበውን አንዳርጋቸው ፅጌ እንዲሁ ጀግና በሉኝ ሲል ልናጅበው አይቻለንም፡፡ የኢሕአፓው በታኝ ዶክተር ዜሮና ጊዜያዊ አጋሩ አዛውንቱ አንጀኛ ደግሞ ራሳቸውን ታጋይ አስመስለው ለማቅረብ በውሸት ሲቀሉና ለሕዝብ ጠላት ምስጢር ያሉትን ሲያቀብሉ በዝምታ ማለፍ አይቻልም፡፡ አሟቸዋል ቢባልም ሕክምና ይፈለግላቸው እንጂ ፖለቲካውን በክህደት ቫይረሳቸው ሊያጠቁ መፍቀድ አይቻልም፡፡

ሌሎች ለዚህ ዕሁፍ የገፋፉኝ ክስተቶች አንድም ስየ አብረሃና የወያኔ የቀድሞ መሪዎች የምስጢር ቴሌ ኮንፈረንስ ማካሄዳቸው መጋለጡ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ዶክተር ገላውዲዮሰ አርአያ የዶክተር ዜሮ አንጃ አዘጋጀሁት በሚለው የጁላይ ሁለት ሲምፖሲየም (ህላዌ ዮሴፍም ይገኝበት ይሆን?!) አንዱ የክብር እንግዳ መሆናቸው ነው፡፡ አቶ ስየ አብርሃ ለአፋቸው እንኳን በወያኔ መሪነት ሳሉ ለፈፀሙት ትመዓት ወንጀል ይቅርታ ሳይጠይቁ በፖለቲካው መድረክ እንደ ሕዝብ መሪ ሊቀርቡ የተደረገው ዘመቻ መንስዔው ደግ አለመሆኑ በፊትም የተጠቀሰ ነው፡፡ እሳቸው፤ገብሩ አስራትና አረጋሽ አዳነ ከአረና ቡድንና አቶ አረጋዊ በርሄ ከተመረጡ የትግራይ ተወላጆች ጋር በቴሌኮንፈረንስ በምስጢር ሊወያዩ መሞከራቸው አምላክ ይባርከውና በዚያ ፅኑ ኢትዮጵያዊ በጌታቸው ረዳ ተጋልጧል፡፡ ይህ ስብሰባ ለምን? በአዲስ አበባ ተቋቋመ ከተባለውና ስዬ አባል ከሆነበት መድረክ፤ ማለትም ወያኔን በመጪው ምርጫ ለማጀብ ከተነሳው ጋር ግንኙነቱስ ምንድነው?  የወያኔ መሪዎችና የትግራይ ተወላጆች የብቻ ስብሰባ የወያኔን ስርዓት ለማዳን ነውን? ወዘተ ወዘተ..አቶ ስዬ ከወያኔነታቸው ፍፁም አልተላቀቁም፡፡ ለዚህም ነው የስውየው ስም የሚነሳው፤ጥያቄም የሚቀርበው፡፡ ዝም በሉና ተወናበዱ፤ ይጫወቱባችሁ ሊባል አይቻልም፡፡ ንቀት ነው በሌላው ሕዝብ ላይ፡፡ ቢሞከርም ልንቀበለው አይገባም፡፡ የዶክተር ብርሃኑና አንዳርጋቸው ፅጌም ስም የሚነሳውም አለምክንያት አይደለም፡፡ የድርጅት ስም ሳይቀር የሰረቁት ምግባረ ፀያፍ አንጃዎችም ዜሮና ቀፎ መባላቸው ስድብ አያሰኝም፡፡

ዶክተር ገላውዲዮስ አርአያ  ኢሕአፓ ነበሩ ሲባል ብሰማም የዚያን ጊዜ ታሪካቸውን በተመለከተ የማወቀው የለኝም፡፡ ለምን ድርጅቱን እንደተዉም በበኩሌ የማውቀው የለም፡፡ ዶክተር ገላውዲዮስን የማውቃቸው ወያኔ ከሆኑ ጀምሮ ነው፡፡ ወያኔን እያዳነቁና ኢሕአፓንም እየተቹ የፃፉትንም መፅሀፍ አንብቤያለሁ፡፡ ዶክተር ገላውዲዮስ የወያኔ መፅሄት የነበረው ኮሜንቴተር አዘጋጅም ሆነው ወያኔን ፕሮፓጋንዳ ሲያስራጩ የነበሩ ናቸው፡፡ ከዚያ እነገብሩ አስራትና ስዬ ከመለስ ሲጣሉ መለስ ዜናዊን ተችተው ወደ ጎን ሆኑ፡፡ ወያኔነታቸውን ሲተቹ ወይም ያለፈ አቅዋሜ ስህተት ነው ሲሉ ግን የሰማ ካለ ሊነግረን ይቸላል፡፡ ዶክተር ዜሮና ዶክተር ገላውዲዮስ የተገናኙት በብተና ነው ወይስ በፀረ ኢሕአፓነት? ለዚህ መልሱ ብዙ ምርምር አይጠይቅም፡፡ ዶክተር ገላውዲዮስ በፀዳ የሕዝብ መድረክ ለመቅረብ በመጀመሪያ ከወያኔነታቸው ወይም ጠባብ ትግራዊ ስሜታቸው መላቀቃቸው

መታወቅ አለበት። መለስ ዜናዊን መተቸት ወያኔን ማውገዝ አለመሆኑን ከስዬ አብረሃ ብቻ ሳይሆን ከነ አቶ አረጋዊም ሁኔታ የምናየው ነውና።

የፖለቲካው መደረክና የሕዝቡ ጎራ ከአንጃና ጠባቦች ይፅዳ!!
ታሪክን መርሳት ይረሳ!!